የስርኣተ ነጥብ ኣጠቃቀም

በዚህ መዝገበቃላት ውስጥ ስራ ላይ የዋሉ ስርኣተ ነጥቦችና የተለያዩ ምልክቶች፡

1. <u>ኣንድ ነጥብ / . /</u>

ሀ. በኣጭሩ የተግፈን ቃል ያመለክታል።

<u>ምሳሌ</u>፡-

ላይ. = ላይንስ

ለ. ከኣንድ በላይ ፍቺ በሚሰጥበት ሁኔታ ከኣገዛ በሂላ በመቀመጥ ኣገባቡን ከፍቺዎች ለመለየት ያገለግላል።

<u>ምሳሌ</u>፡-

ግንባር (ግምባር) ስ 1. ወጉር ከበቀለበት የራሲ ክፍል በታች ከኣይን በላይ ያለ የሰውነት ክፍል። 2. ፊት ለፊት። *ቤቱ ግንባር ላይ ነው ያለው።* 3.(ዘይ.) እድል፡ ገድ። *ጥሩ ግንባር ኣለው።*

2. ሰያፍ መስመር ወይም ሀዝባር (/)

ሀ. ረዘም ያለ ቃልን ወይም ሃረግን ለማሳጠር ያገለግላል።

ምሳሌ፡

ት/ሚ = ትምህርት ሚኒስቴር

ለ. አንድን ሃሳብ የሚወክሉ ወይም የሚገልፁ የተለያዩ ቃላት ሲኖሩ ወይም አንድን ፍቺ ለማብራራት የሚደረደሩ የተለያዩ አስረጂዎች ሲኖሩ ወይም አንዱን ቃል የሚተካው ሌላ ቃል ከለ ተተኪው ወይም አማራጩ ቃል ወይም አስረጅ በሰያፍ መስመር እየተለየ ይቀመጣል።

ምሳሌ፡-

ሆዱ አረረ /ቆሰለ/ ተቃጠለ ተናደደ።

3. የኮከብ ምልክት / * /

ፍች ወይም ትርጉም ባልተሰጣቸው ቃላት አናት ላይ በስተግራ በኩል ይቀመጣል። እንደነዚህ ያሉት ቃላት በስሩት የማይታወቁ ወይም በአገልግሎት ላይ የሌሉ ወይም ለውልድ ቃላት መነሻ ናቸው ተብለው የግምት ትርዕ የተሰጣቸው ቃላት ናቸው።

ምሳሌ፡-

***ወለበ**

ወለባ ቅ ቀትረ ቀሊል፡ ነጠላ፡ ሾላካ፡ ጥላ ቢስ ።

ውልብ አለ ግ ታይቶ ጠፋ፡ ከመቅፅበት ሽው ብሎ አለፈ ።

4. የጥቅስ ምልክት / " " /

ከሌላ ፅሁፍ እንዳለ የተወሰደ ገለፃን ወይም አረፍተ ነገርን ወይም በተመልከት ጊዜ (በማጣቀስ ጊዜ) የሚተኮርባቸውን ቃላት ለማመልከት ያገለግላል። እንዲሁም አልፎ አልፎ በፍቺ ውስጥ የሚጠቅምን አማራጭ ቃል ለይቶ ለማመልከት ያገለግላል።

ምሳሌ፡-

በ**ሆ** "ቦካ" ስር "ቤት"ን ተመ.

ተርጓሚ ስ 1. በአንድ ቋንቋ የተነገረውን ቋንቋውን ለማያውቅ ሌላ አድማጭ የሚተረጉም፡ "ትርጁማን"ም ይባላል።

5. ሰረዝ / - /

ሀ. አንድ ከፊሉ ቃል ወይም ምእላድ ወይም ያልተሟላ ቃል ሲኖር ከቀሉ ቀድሞ ወይም ቀጥሎ ከንኑ በመቀመጥ ያ ቃል ከሌላ ቃል ጋር የሚጣመር መሆኑን ለመጠቆም ያገለግላል::

ምሳሌ:-

ስነ-

ፀረ-

- ነክ

- አስተኔ

6. ነጠብጣብ / ... /

በመዘርዘር ገለፃ ጊዜ ሁሉንም ነገሮች ከመግለፅ ይልቅ የተመሰኑትን ብቻ ጠቅሶ ሌሎችም እንዳሉ ለመጠቆም ይገባል::

ምሳሌ :-

ወለድ አግድ ስ አበዳሪዎች በገንዘብ ቅርፃ ወይም አራጣ ፋንታ የተበዳሪን ቤት፡ መሬት፡... በመያዝ የሚጠቀሙበት የብድር ውል አይነት ::

7. አራት ማእዘን ቅንፍ / [ ] /

በተናጠል ወይም ከሌላ ቃል ወይም ምእላድ ጋር በመጣመር የሚነገር ቃል ሲኖርና ቃሉ (ያልተጣመረው) ብቻውንም መነገር የሚችል መሆኑን ለማሳየት ሲፈለግ ተጣማሪው ቃል በአራት ማእዘን ቅንፍ ውስጥ ይቀመጣል::

ምሳሌ:-

ቁምጣ [ሱሪ]

ሸራ- [ጫማ]

[የ] ብርድ ልብስ

8. ቅንፍ / ( ) /

ሀ. በተለያየ ቅርፅ ወይም አጠራር የሚነገር ስም ሲያጋጥም እንደመደበኛ የሚቆጠረው ወይም አንደኛው ቃል ብቻ ከቅንፍ ውጪ ሆኖ ሌላው ቃል በቅንፍ ውስጥ ይቀመጣል::

ምሳሌ፦

ቢላ (ቢላዋ ÷ ቢላም)

ቀዥቃዣ (ቀዥቀዥ)

ሁልጊዜ (ሁሌ)

ሙቀጫ (ሙገጫ)

ለ. ለየት ያለ የብዙ ቁጥር ቅርፅ ያላቸው ቃላት ካሉ የብዙ ቁጥሩ አንዳንዴም የነጠላ ቁጥሩ ቅርፅ በቅንፍ ውስጥ ይቀመጣል።

ምሳሌ፦

ካህን (ብ.ቁ. ካህናት)

ህፃን (ብ. ቁ. ህፃናት)

ልኡል (ብ. ቁ. ልኡላን)

መኳንንት (ነጠ. ቁ. መኮንን)

መ. የሚፈቱት ቃላት ተጨማሪ መግለጫ የሚያስፈልጋቸው ሆኖ ሲገኝ ከቃላቱ ፍቺ በፊት መግለጫው በምህፃረ ቃል ወይም ሙሉ ቃሉ እንዳለ በቅንፍ ይቀመጣል።

ምሳሌ፦

ለብላቢ ቅ (የአራዳ አነ.) ጠጪ÷ ሰካራም።

በልቃጣ ቅ (ነውር÷ ስድብ) 1. ሃፍረተ ስጋዋ እንዳይታይባት ጥንቃቄ የማታደርግ÷ በርጋዳ። 2. ስነስርአት የሌላት÷...።

ነነዌ (ነይ ነይ) ስ (ኢ. አ. ተ. ቤ.) ከሁዳዴ ፆም መባቻ አስራ አራት...።

ረ. የተሰጡት ፍቺዎች ተጨማሪ መግለጫ ወይም ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው ሆኖ ሲገኝ ከፍቺው በፊት÷ በፍቺው መካከል ወይም ከፍቺው በሃላ መግለጫው ወይም ማብራሪያው በቅንፍ ውስጥ እንዲቀመጥ ይደረጋል።

ምሳሌ፦

ባዶ ቤት ስ 1. ምንም ነገር (ምግብ÷ መጠጥ÷ ገንዘብ÷ ...) የሌለበት ቤት።

2. ሰው የሌለበት ወና ቤት።

በረራ ስ ጉዞ (የአውሮፕላን)።

ተቻቻለ ግ 1. (ክፍያ÷ ወጪ÷ ኪሳራ÷ እዳ÷...) ተጣጣ÷ ተብቃቃ÷ ተካካሰ።